# ምድብ አምስት (ከ10ኛ — 12ኛ) ክፍል

## 34 ኛ ሳምንት

## መንፈስ ቅዱስ - የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች

**የትምህርቱ ዓላማ**

- ይህ ትምህርት በተከታታይ እየተማርነው ያለው ትምህርት ቀጣይ ክፍል ሲሆን፤
- በዛሬው ትምህርታችን ስለመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እንማራለን፡፡

**መግቢያ**

- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሰማያዊ ስጦታዎች ስለሆኑ የእግዚአብሔር ውድ ስጦታዎች ናቸው፡፡

**የሚጠኑ ጥቅሶች**

- *"የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል"* ዮሐ 16÷13
- *"የጸጋ ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው…ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል፡፡"*1ኛ ቆሮ 12÷4-8

**ምንባብ**

- 1ኛ ቆሮ 12 - 14 ፣

**ትምህርቱ**

- ከላይ ኃይልን እስኪያገኙ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ ክርስቶስ ሲያዛቸው፡፡ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ምስክር ሆና እንድትኖር የሚያስችላት የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ እንድትቀበል የተነገረ አስፈላጊ አዋጅ ነበር፡፡ይሄም ሆኖ መንፈስ ቅዱስ ከሰዎች ፍላጎትና ነፃ ምርጫ ውጭ አይሰራም፡፡
- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ከእግዚአብሔር የሚሠጡ ናቸው እንጂ ከሰው ተፈጥሮኣዊ ችሎታ ወይም ብቃት የሚመነጩ አይደሉም፡፡ነገር ግን ደግመን የምናጸናው የእግዚአብሔር ሥጦታ ብቻ መሆናቸውን ነው፡፡ ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ ላይኛይቱን ጥበብ (ማለትም የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ) እና ምድራዊቱን ጥበብ ልዩነት ገልፆልናል፡፡ *"ከእናንተ ጥበበኛምና አስተዋይ ማነው? በመልካም አንዋዋሩ ስራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ፡፡ ነገር ግን መራራ ቅንዓትና አድመኛነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ አትመኩ በእውነትም ላይ አትዋሹ፡፡ ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም ነገር ግን የምድር ነው የሥጋም ነው የአጋንንትም ነው ቅንዓትና አድመኛነት ባሉበት ስፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ስራ ሁሉ አሉና፡፡ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፣በኋላም ታራቂ፣ገር፣ እሺ ባይ፣ ምህረትና በጎ ፍሬ የሞላባት ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት፡፡"* ያዕ. 3÷13-17
- ይህች ሰማያዊ ጥበብ የምትሠጠው ከመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ይሄንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ገልጦታል፦*"የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ ነው፤ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤ አሰራርም ልዩ ልዩ ነው ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል፡፡ ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፣ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ ለአንዱም ተዓምራትን ማድረግ ለአንዱም ትንቢትን መናገር፣ ለአንዱም መናፍስትን መለየት፣ለአንዱም በልዩ ልዩ ኣይነት ልሳን መናገር፣ለአንዱም በልሳን የተናገረውን መተርጎም ይሰጠዋል፤ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ደርጋል፡፡"* 1ኛ ቆሮ 12÷4 - 11
- ስጦታዎች በሦስት ይከፈላሉ፡-

1. **የመናገር ስጦታ**

- መንፈስ ቅዱስ ትምህርቱን ይመራል የሚናገሩትንም ቃል ለመምህራን ይሠጣል፡፡*"የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል"* ዮሐ 16÷13
- ትንቢትም በማንበብ እና በብልሀት አይቻልም፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ነው እንጂ፡፡ *"መንፈስ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ስንኳ ሳይቀር ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር በመንፈሱ በኩል ገለጠው፡፡"* 1ኛ ቆሮ.2÷10
- በልሳኖች መናገር ይህ ስጦታ ሰባክያንን ለማገዝ የሚሠጥ ነው፡፡ መናገር በማይችሉትና ሕዝቡ በሚናገረው ቋንቋ እንዲያስተምሩ ነው ጥቅሙ፡፡ *"በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፣ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር፡፡ ይህ ድምፅ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ፣ እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለነበር የሚሉትን አጡ፡፡"* የሐዋ.ሥ 2÷4-6

2. **ስለ እግዚአብሔር የማወቅ ጸጋ**

- በእውቀት ማስተማር ስለእግዚአብሔርም ማወቅ ይህን ጸጋ ያገኙ አበው መጻሕፍትን ተርጉመዋል፡፡ ስለእግዚአብሔር ኀልውና አንድነትና ሦስትነት ምስጢርም "እንደተሠጣቸው ጸጋ መጠን" አብራርተው አስተምረዋል፡፡ ሐዋርያው ስለዚህ ሲገልፅ *"የክብር አባት ጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ፡፡ ይህም የልባችሁ ዓይኖች ሲበሩ የመጥራቱ ተስፋ ምን እንዲሆን በቅዱሳንም ዘንድ ያለው የርስት ክብር ባለጠግነት ምን እንዲሆን ለምናምነዉ ከሁሉ የሚበልጥ የኃይሉ ታላቅነት ምን እንዲሆን ታውቁ ዘንድ ነው፤"* ኤፌ 1÷17-18 በጥበብ ማስተማር…ከእግዚአብሔር ጋር ስመኖር ነው፡፡1ኛቆሮ14÷1-4

3. <u>ተግባራዊ ስጦታዎች</u>

- ተዓምራትና ኃይልን ማድረግ፣ *"ለአንዱም በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ ለአንዱም ተዓምራትን ማድረግ..."* 1ኛ ቆሮ 12÷9

- ሰዎችና ፍላጎቶቻቸውን በፍቅር ማገልገል፡፡1ኛ ቆሮ 13 ÷1-8

***ማስታወሻ***

(1) ለአማንያን ስለሚሰጣቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች የሚገልጡ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አሉ፡፡በስፋትና በጥልቀት የመንፈስ

ቅዱስን ስጦታዎች የሚገልጹልን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ግን ሦስቱ የ1ኛ ቆሮንጦስ ክፍሎች ናቸው፡፡1ኛ ቆሮ 12,13 እና 14

(2) እነዚህን የመጽሐፍ ጥቅሶችና በቤተክርስቲያን ስለመንፈስቅዱስ ጸጋ የተጻፉትን አንብቡ፡፡

***ምን ተማርን***

(1) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ለመቀበል ወደ እግዚአብሔር መጸለይ አለብን፡፡

(2) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለአንድ ሰው ሲሠጠው፡፡ ለተለያዩ ምክንያቶች ነው፡፡ ዋነኛው ምክንያትም ቤተክርስቲያንን እና የእግዚአብሔርን

መንግስት ለማሳደግ ነው፡፡**ለምሳሌ** ሐዋርያት በልሳን መንገር የተሰጣቸው ዋና ምክንያት በተለያዩ ሕዝቦች ቋንቋዎች እንዲያስተምሩ፡፡

***<u>ለእኛ የሆነ የእግዚአብሔር ፍቅር</u>***

- ለእኛ በሆነው በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ እርሱ እኛን የሚቀጥረን የራሱ ክፋይ አድርጎ ነው፡- ***"እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፡፡"*** ዮሐ 15÷5

- እንዲህም ብሎናል፡- *" . . . ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን . . ."* ኤፌ 5÷30፡፡ ወይም ደግሞ እርሱ ራስ ሲሆን ቤተ ክርስቲያን ደግሞ አካሉ ናት፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፡- *"... በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ፡፡"* (ዮሐ 15÷4) ብሏል፡፡

- እኛን አስመልክቶ ለአአባቱ ሲናገርም ይህን ብሏል፡- ***"እኛም አንድ እንደሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእርሱ አንተም በእኔ ስትሆን በአንድ ፍጹም እንዲሆኑ ..."*** ዮሐ 17÷22

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ *" ... ***ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች*** ..."* (2ኛ ጴጥ 1÷4) ተብሎ የተጻፈውና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር የሚያሳየው አገላለጽ ምንኛ ድንቅ ነው! ከዚሁ በተመሳሳይ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፡- ***"... የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችን ጋር ይሁን፡፡"*** 2ኛ ቆሮ13÷4፡፡ በእርግጥ ይህ ኅብረት የሥራ እንጂ የአካልና የባሕርይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ራሱና ስለ ወንድሙ ስለ ሲላስ ሲናገር ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነን በሏል፡፡

- የእግዚአብሔር ፍቅር ለእኛ ካለው አሠራር አንዱ በእርሱና በእኛ በሰዎች ዘር መካከል የዳበረው ወዳጅነት ነው፡፡ አብርሃም ***"ኣርከ እግዚአብሔር"*** ወይም ***"የእግዚአብሔር ወዳጅ"*** ተብሎ ተጠርቶአል፡፡ስለሄኖክም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፡- ***"ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ወስዶታልና፡፡"*** ዘፍ5÷24፡፡ሙሴም ቢሆን ከእግዚአብሔር ጋር በተራራው ላይ ለአርባ ቀናት ቆይቶአል፡፡አሥራ ሁለት ሐዋርያትም ሌሎች ምሳሌዎቻችን ናቸው ፣ኢየሱስ ክርስቶስ ከእነርሱ ጋር የነበረው ኅብረት ልዩ ነበረና፡፡

- እግዚአብሔር ደስታውን ከሰው ልጆች ጋር ማድረጉም ድንቅ ነው፡፡እሱ የማይወሰን አምላክ ሆኖ በሚወሰኑት በሰዎች ዘንድ ትሕትናውን በመግለጥ ከእነሱ ጋር ኅብረት ፈጥሮአል፡፡ ለእነርሱ በመገለጠም ቃል በቃል አነጋግሯአቸዋል፡፡

- ታሪክ እንደሚነግረን እነዚህ ሁሉ የእንክብካቤ አስደናቂ መንገዶች የተገለጡት እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ ነው፡፡ ለምሳሌ ፡- የቀይ ባሕር ለሁለት መከፈል፣በምድረ በዳ የወረደው መና ፣ከጭንጫ ዓለም የፈለቀው ውኀ፣በረሀበ ዘመን የኤልያስ መጠበቅ፣ ጴጥሮስን ከእስር ቤት - ዳንኤልን ከአናብስት ጉድጓድ - ሠለስቱ ደቂቅን ከእቶን እሳት ማውጣትና ሌሎችም ማብቂያ የሌላቸው የእንክብካቤና የጥበቃ ታሪኮች ለእኛ ተደርገውልናል፡፡

- እግዚአብሔር ለኛ ካለው ፍቅር የተነሳ ምልክት ይሆኑን ዘንድ እነዚህን ቃል ኪዳኖች ለእኛ ምልክቶች አድርጎ ስጥቶናል ፡-***"እነሆ እኔ በእጄ መጻፍ ቀርጬሻለው፣. . ."*** (ኢሳ 49፡16 )፣ ***"የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቆጥሮል፡፡"*** (ማቴ 30፡10)፣ ***"አዲስም ልብ እሰጣችኋለሁ. . ."*** (ሕዝ 36፡ 26 )፣ ***". . . ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም፡፡"*** (ጦሐ 10፡29)፣ ***". . . ስፍራ አዘጋጅላችው ዘንድ እሄዳለሁና፣. ."*** (ዮሐ14፡2)፡፡

- የተሰጡን ስጦታዎች ሁሉ እግዚአብሔር ለሰው ያለውን ፍቅር የሚገልጡ ናቸው፡፡

- የዘላለማዊነት ስጦታ፣ በእርሱ ክብር በእካል የሚሆን የትንሳኤ ስጦታና ሌሎችም ብዛት ያላቸው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ሁሉ በእግዚእብሔር ፍቅር የተባረኩ ናቸው፡፡

**ይቆየን፡፡**